# የበርማ ምርጫና ትምህርቱ

ከመላኩ ይስማው

በርማ በተባለችው የእስያ ሀገር ሰሞኑን በተካሄደው ምርጫ ወታደራዊው ኣምባገነን ኣገዛዝ አቸናፊ መሆኑ ታውቋል። የተጭብረበረ ምርጫ ነውና ነው። በምርጫ አትሳተፉ የተባለውን አልሰማ ብለው የተሳተፉትም ከሺ 500 በላይ ወንበር ውስጥ 16 ብቻ አግኝተዋል፤ ተሸንፈዋል። የበርማው አፋኝ አገዛዝ ከወያኔ በተሻለ ምን ይሉኛል የሚል ጭንቀት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ሁሉን ወንበር አሸነፍኩ ማለቱን አልመረጠም።

የበርማ ሁኔታ ትምህርታዊነት ተጠቃሽ የሆነው አንዱ ዋና ምክንያት ወይዘሪት ብርቱካን ሚዲቅሳን ከበርማዋ ዋናና ዝነኛ ተቃዋሚ ኣን ሱን ኪ ጋር ማመሳሰል የሚወዱ ብዙዎችም በመኖራቸው ነው። ይህ ቦሎቄን ባቄላ የማለቱ አባዜ የወያኔ ተቀጣሪ የሆነውን ክህደቱን ማንዴላ ያስኘ መሆኑንም የታዘብነው ነው። በርማና ኢትዮጵያን ማመሳሰል የተጀመረው ወይዘሪት ብርቱካንን ከበርማዋ ዝነኛ ታጋይ ኣንግ ሱን ቺ ጋር ማመሳስል በመጧጧፉ የተነሳ ነው። ብርቱካንና ሱን ቺ በፖለቲካም ሆነ በተመክሮ ከቶም የሚገናኙ አለመሆናቸው ግልጽ ነው። ብርቱካንን ለማወደስ ለምን ሱን ቺ መባል እንዳለባት ግልጽ አይደለም። ራሱዋ በራሱዋ በአቅዋም ሆነ በሰራችው መመስገን የምትችልና የሚገባትም ናትና። የሀገራችን ዘመናዊ ፖለቲከኞች ወይም ግንባር ቀደም ደቀ-መዘምራናቸው ግን በሀገራቸው ታሪክም የሚኮሩ አይደሉምና ሸዋረገድ ተክሌ፣ አበራሽ በርታ ወዘተ ማለት ሲችሉ ውቅያኖስ ኣቋርጠው በመሄድ ሱን ቺ ወይም ማንዴላ አለዚያም ጋንዲ ማለቱ ይቀናቸዋል። በሌላው ኮከብ ብርሀን መጓዝን ይመርጣሉ። በድቅድቁ የሀገራችን የፖለቲካ ሰማይ ላይ እራሳቸውን አቃጥለው ያበሩልንንና እያበሩልን ያሉትን ኢትዮጵያዊያን ከዋክብት ማየት አይሹም።

አዎ! ሱን ቺ ለ20 ዓመታት በቤቷ ታግዳ ቆይታለች። በግል ኑሮዋ ሳይቀር ሁኔታው ጫና ቢያመጣባትም ጸንታ መቆየቷና ለሀገርዋ ዜጎችም አርአያ ሆና መቆየቷ የተረጋገጠ ነው። የበርማ ወታደራዊ አገዛዝ ከ 400 በላይ የድርጅት

አባሎቿን አስሮ ከማቆየቱ ሌላ የምርጫውንም ህግ በቁጥጥሩ ያስገባ በመሆኑ ሱን ቺ ድርጅቷ በምርጫው እንዳይሳተፍ ወይም ማዕቀብ እንዲያደርግ ግልጽ አቋዋም ይዛ ነበር። ሁናቴዎች ለሕዝብ መጥፎ በሆኑበት በምርጫ አለመሳተፍ ራሱ ትግል መሆኑን ላልተረዱት የሀገራችን ፖለቲከኞች ትምህርት ሊሆን የሚገባው ነው። ማዕቅብ ማድረግ ስህተትና ሽንፈት ነው ለሚሉት ማለት ነው። ሱን ቺን ከድተው ሌላ ድርጅት የመሰረቱትም ጥሪዋን አንሰማ በማለት በምርጫው ተሳትፈው እንደ እኛው ተቃዋሚ ተብየዎች ኩንታል ሽንፈትን መሸከም ተገድዋል። ወታደራዊው አገዛዝ በይምሰል ምርጫ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት መስረቁ ከየአቅጣጫው ተቃውሞ ስላስከተለበት አጀንዳ ለማስቀየር ጭምርም ሊሆን ይችላል የፈታት። ሱን ቺ ግን አገዛዙ ቢፈታኝም በፖለቲካ ትግሌ እቀጥላለሁ ብላ ውሳኔዋን ከወዲሁ በድፍረት አስታውቃለች። ቋንቋም፣ የትግሉ ውልም አልጠፋትም። ወይንም ሌላ መሰል የማጭበርበሪያ የምርጫ ድራማ እስከሚያዘጋጅ እጠብቃለሁ አላለችም። ትግሉንም እራሳቸውንም ከአሸዋ ውስጥ ቀብረው ሌላ ወያኔያዊ ምርጫ ካምስት ዓመት በሁዋላ እስከሚዘጋጅ ለሚጠብቁት ለኛዎቹ "የሰላም" ፖለቲካ መሪዎች እና ተከታዮቻቸው ትምህርት ቢሆናቸው።

የሱን ቺና በአጠቃላይም የበርማ ተመክሮ የንቃትና ጥራት፡ የጽናትን ወሳኝነት አስፈላጊነት ያስተምረናል። ኢ.ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ በሰፈነበትም ፍትሓዊ ምርጫን መጠበቅ ሞኝነት መሆኑን ዳግም ያረጋግጣል። ሱን ቺ ስትታሰር እንግሊዛዊ ባሏ ጥሏት ሄዷል። ነጋ ጠባ የወታደራዊ አገዛዙን ውሳኔ እንድትቀበልና ተቃውሞም እንድታቆም ልዩ ልዩ ተጽዕኖ ተደርጎባታል። ግን አልተበገረችም። ብትለቀኝም የፖለቲካ ትግሌን አላቆምም እያለች ነበር። ተንታኞች እንደሚሉትም በትግልና በውጭ ሃይላት ግፊት ከተፈታችም በሁዋላ ለእራሷ የማያንቀሳቅስ ጋዲ ሳታስገባ በነፃ እየተንቀሳቀሰች የሀገሯን ሕዝብ ለማነጋገር ቆርጣለች። የትግል ፍልሚያዋን ልትቀጥል። ከድተዋት ተገንጥለው ወይም አንጃ ሆነው በምርጫ የገቡትም በአሰቃቂ ሽንፈት ተዋርደዋል። ሕዝባዊው አጋርነትም አልተቸራቸውም።

በተቃራኒው ደግሞ ልትፈታ ነው የሚለው ዜና እንደተነገረ ጀምሮ የሀገሯ ሕዝብ "እረጅም እድሜ ለሱን ቺ!" ሲል ነው የተስተዋለው። ለ20 ዓመታት መታሰሯና

የፀና አቋም መያዟም ሌላው ቀርቶ በእነኝህ ዓመታት ውስጥ የተወለዱት ወጣቶችንም ጨምሮ ብዙሀኑ እንዲከተላት፣ መሪያችን እንዲላት አደረጋት እንጅ አላስረሳትም። ከልቦናቸው አብሪ ኮከብነቷን አላደበዘዘውም። በምዕራባዊያኑ መንግሥታትም ሆነ በተባበሩት መንግሥታት ማህበርም አስከበሯታል።

ወደእኛ ስንመለስ እስካሁንም የሀገር ማዳኑ ዴሞክራሲያዊ ትግላችን ያስከፈለን ዋጋ ከመታሠር፣ በአካልም ሆነ በሥነ-ልቡና ስቃይ ከመማቀቅ በላይ ነው። የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉና በመክፈል ላይ ያሉ አያሌ የትግል ፊርጦች አሉ። ግቡን እስኪመታም ድረስ እንደዚሁ መሰል ዋጋ ማስከፈሉ የግድ ነው።

እናም የትግል መሪዎቻችን ይህን ዋጋ ለመክፈል የቆረጡና ሞታችንን የሚሞቱ መሆን አለባቸው። ተከትለናቸው ስንሞትም ሞታችንን እየሞቱ ትግሉን የሚቀጥሉ መሆን አለባቸው። ተከታዮቻቸውን የሚገርፈው ጅራፍ ወይም የሚገድለው ጥይት ሲጮህ ወገቤን የሚሉ፣ ገራፊዎቹና ገዳዮች ሲቆጧቸው፣ ጠዋት የተናገሩትን ከሲያት ላይ በይቅርታ የሚያጥፉ ከሆነ የትም አያደርሱን። በእቅድ ሀገርና ሕዝብ ለሚያጠፋው ፀረ-ኢትዮጵያ የወያኔ አገዛዝ "ሳያውቁ ነውና የሚያጠፉት ይቅር በላቸው!" ብለው የሚፀልዩ ሳይሆን "ሳያጠፉን እናጥፋቸው!" የሚሉ ቁርጠኛ መሪዎች ፣ ጀግኖች ነው የሚሻው ትግላችን።

እኛ ግን የምንሻቸውን መሪዎች መለኪያ ሚዛናችንን ከዚህ እውነታ ጋር እያገናዘብነው አይደለም። ጸጋዬ ገብረመድህን አርአያ "ጦቢያ" መጽሔት፣ 2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5 እትም ላይ እንዳሉት፡

*ሟች ደራሲና ጋዜጠኛ መንግሥቱ ገዳሙ በድል በዓል አከባበር ላይ ኒሻናቸውን ከደረታቸው ላይ ገጥግጠው "እትት" እያሉ በመንዘፍዘፍ የሚፎከሩትን አባቶችና እናቶች "አርበኞች ነን ልትሉ ነው? ጀግኖች እኮ ሞተዋል ...ተቀብረዋል ... ችግሩ መቃብራቸው አይታወቅም እንጂ?" ይል ነበር። ዓይናችሁ ዓይናችሁን ለማየት፣ ሕሊናችሁ ሕሊናችሁን ለመመርመር ካልቻለ ጀግኖች አይደላችሁም ለማለት ስለፈለገ ይመስለኛል። አንድ ጊዜ ከሙታን ዓለም ብንጠራው መንግሥቱ ንዋይም፣*

*መንግሥቱ ገዳሙም ብዙ ብዙ በተናገሩ ነበር። በመኖር ያረጋገጥሁት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሕይወት ውስጥ እውነት ለመናገር የሚፈልጉ ሰዎች መድረክ ፓርላማ (ምክር ቤት) አለመሆኑን ነው። ... የብዙዎች እውነት ተናጋሪዎችና እውነት አራማጆች ሥፍራ እስር ቤት ይመስለኛል። ምክንያቱም ለዘመናት የኢትዮጵያን ትክክለኛ ሥዕል የሚያቀርቡ፣ የፍትሕንና የሰብአዊ መብትን መረገጥ፣ የዲሞክራሲን የለበጣን ቋንቋ መሆን የሚናገሩ ሰዎች እንደ አደገኛ እንሰሳትና አራዊት የሚጠበቁት በእሥር ቤት ነው። ...*

ያውም ከቅርቦቹ ጀግኖቻችን እንደ እነ ተስፋዬ ታደሰ፣ አሰፋ ማሩ፣ ሽብሬ ደሳለኝ ወዘተ ወዘተ በየአደባባዩ ካልተገደሉ። እንደ ዱር አውሬ በየእስር ቤቱ ያሉትን ጀግኖች እግርና እጅ የጠፈረው ሰንሰለት፣ ደማቸው የፈሰሰው ሰማዕታትን የተጫነው መቃብር ላይ ነው የትግላችን መሪ ኮከብ ያለው። ማስተዋል ካልተሳነን በስተቀር። ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ጸጋዬ፣ ከ15 ዓመታት በፊት በሌላ መጣጥፋቸው፡

*እኔ እንደሚሰማኝ ግን ትልቁ እንቅፋት ሃጢአታችን ነው። ሳይታሰብ ከጠላት (ፋሽስት) ወዲህ ያለው የኢትዮጵያ ትውልድ "ጀግና" የሚገድል፣ ጀግና የሚጠላ፣ በጀግና ደም የታጠበ ሆኖአል። እርግጥ ጀግኖቻችንን የገደሉት መንግሥትና ወታደሮች ናቸው። እኛ ደግሞ ጀግኖቻችንን አላዳናቸውም። ምናልባትም ጀግኖቻችን ሲታሰሩ፣ ሲገደሉ፣ ለሕዝብ ነፃነት የቆሙ ወገኖችን አበሳ ሲቀበሉ፣ በመንግሥት ሲሰቃዩ፣ ከአምባገነኖች ጋር ቆመን የድጋፍ ሰልፍ ወጥተናል። ... ጀግና ከመግደል በቀር ሙያ የሌለን ይመስል፣ ደም በእጃችን አለ። ንጹሕ የጀግና ደም፣ ወፍራሙ ኢትዮጵያዊ ደም በእጃችን አለ። ጠመንጃ በእጃችን ባይኖረንም ለምን ሞቱ እንኳ አላልንም። ስለዚህ ከገዳዮች ጋር ሁላችንም ተባብረናል። ባለ ሱሪ ወላድ ኢትዮጵያ ጀግኖቿን ተንከባክባ አታውቅም። "የገደለሽ በላ" እንጂ የሞተልሽ በላ የሚል ሐቅ የለንም። ... ከአድማስ ባሻገር ከሚታዩን ተራሮች የበለጠ ግዝፈት ያላቸውና — ለዚህች ሀገር መከታ ናቸው የሚባሉትን ወገኖች ጨፈጨፍን። የኢሕአፓ ተከታዮች ናቸው እየተባሉ በየአደባባዩ የተገደሉትንና የተጣሉትን ወጣቶች "አብዮታዊ መንግሥታችን" ስንለው የነበረው ሥርዓት ራሱ ሲጨፈጭፍ ዝም ብለን መመልከት ብቻ ሳይሆን ግልጽም ስውርም ድጋፍ*

*ሰጥተነዋል። ወያኔ በጫካ፣ ደርግ በከተሞቹ እኒህን አበባዎች ሲቀጥፉ ድምፃችንን አላሰማንም። መተባበር ብቻ ሳይሆን ቀጥታ የወንጀል ተሳታፊነት ስለመሰለኝ ትውልዱን ራሱን ነፍሰ ገዳይ ትውልድ ለማለት ደፍሬአለሁ። ወንጀል በመሥራትም፣ አይቶ በማለፍም ይፈጸማል። ስሜታዊ ለሆነው አገላለጼ ደግሞ ይቅርታ እጠይቃለሁ። አንድ ሌላ ጥያቄ ለመጠየቅ የምገደደው የሚሞትልንና የሞተልንን የምንገድልበት ሁኔታ የለምን? የሚል ነው።*

በማለት የጠየቁትን ጥያቄ አሁንም መልስ አልሰጠነውም። ወያኔን የመሰለ ካልጠፋ የሚያጠፋ ጸረ-ኢትዮጵያ ጠላት እያለ፣ ዛሬም እነኛን ትላንት የተቀጠፉትን አበባዎች ከመቃብራቸው ዳግም ለመግደል ከተነሱ ጋር እንተባበራለን። የትላንት ገዳዮቻቸውን፣ አሳሪዎቻቸውንም ለምን ገደላችሁ አሰራችሁ አንልም። ጭራሽኑም የትላንት ገዳዮቻቸውን፣ አሳሪዎቻቸውን በሙሉ እቅፍ እየተቀበልን በሽልማትነት የ"ምሩን" ገጸ በረከት እንሰጣቸዋለን። የትላንት ገዳዮቻቸው፣ አሳሪ፣ ገራፊዎቻቸው ስላደረጉት ኢሰብአዊ ድርጊት ያለእፍረት በጨው ታጥበው ሲጽፉ፣ የወንጀል ታሪካቸውን በመግዛት/በማሻሻጥ እንጠራቸዋለን። የግፋቸው ሰለባዎችን መቃብር በማጥፋት፣ የታሰሩበትንና አሁንም ታስረውበት ያሉበትን ሰንሰለት በማጥበቅ፣ የሀገራችንና የሕዝባችንን መከራ እናራዝማለን። ከእነሱም ላይ ያለውንና ሕዝባዊ ትግሉ ግቡን እንዲመታ የሚመራንን ፋና ወጊ ኮከብ ላለማየት ዓይናችንን እንጨፍናለን። የትግሉ ዳፍንት እኛው ጋር ነው ያለው፣ መፍትሄውም እኛው ጋር ነው። ትግሉ ከሚጠይቀው እውነታ አንፃር የድርጅቶችንም ሆነ የግለሰቦችንም መለኪያ በማስተካከል ለሁሉም እንደ ዋጋው ዋጋ መስጠት። እንኳን መምቻ፣ ማስፈራሪያ የማይሆን አገዳ እየመረጥን ትግሉን በማወላከፍ ፈንታ፣ ቢመቱበት የሚያሳምም፣ የሚያደማ፣ ቢመክቱበት የሚያድን ጥሩ ዱላ ጨብጦ ከትግሉ መግባት። ባንገባ እንኳ ለሽንፈታችን ሳይሆን ለድላችን ማፋጠኛ በሚሆን መንገድ ማገዝ።